# የአቡነ ሓራ ድንግል መድኃኔዓለም ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ

**በዳላስ/ፎርት ዎርዝ፣ ቴክሳስና በአሜሪካን ለሚኖሩ አባላትና ደጋፊዎች የሚያገለግል ደንብ።**

**ሚያዝያ 4 ቀን 2012 ዓ.ም.**

**(April 12, 2020)**

# የአቡነ ሓራ ድንግል መድኃኔዓለም ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ

## ማውጫ


ሽፋንና ሕገ ደንብ የርቀቀበት ቀን....................1

ማውጫ....................2

መግቢያ፣ መልእክት፣ ከገዳም አባቶች የተላለፈ ቅድመ ዕይታ ገዳም....................3

አንቀጽ 1 የማኅበሩ ስምና አድራሻ....................3&4

አንቀጽ 2 የማኅበሩ አመሠራረት....................4

አንቀጽ 3 የማኅበሩ የአጭርና የረጂም ጊዜ ዕቅድ....................4

አንቀጽ 4 የማኅበሩ ራዕይ....................4

አንቀጽ 5 የማኅበርተኞች መብትና ግዴታ....................4&5

አንቀጽ 6 የማኅበሩ አደረጃጀትና መዋቅር (ቻርት)....................5

አንቀጽ 7 ሥልጣንና ኃላፊነት (ጠቅላላ ጉባኤ)....................5&6

አንቀጽ 8 የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ፣....................6

8፡1 የመስተንግዶ ኮሚቴ፤....................6

8፡2 የማኅበራዊ ግንኙነት፡-....................6

8፡3 ተዐምር ወመዘክር....................6

8፡4 የማኅበሩ አጠናካሪ ኮሚቴ፣....................6

አንቀጽ 9 ተቆጣጣሪ....................7

አንቀጽ 10 የመገናኛ ዘዴዎች....................7

አንቀጽ 11፣ ማጠቃለያ....................7

የመተዳደሪያ ደንብ አውጪ ኮሚቴ ፊርማ።....................7

# የአቡነ ሓራ ድንግል መድኃኔዓለም ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ

## መግቢያ

አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አሜን።

የአቡነ ሓራ ድንግል መድኃኒዓለም ማኅበር አገልግሎት የጀመረው እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ጥቅምት 27 ቀን 2006 ዓም ሲሆን መስራቾቹም ከመንዝና ግሸ አውራጃ ልዩ ስሙ ይገም ወይም ማማ ምድር ከሚገኘው የአቡነ ሓራ ድንግል ገዳም በሚመጣው እምነት የተፈወሱ በዳላስ (ቴክሳስ) አካባቢ የሚኖሩ ምዕመናን ናቸው።
ማኅበሩ ፈውስና በረከት የሚታይበት ማለትም የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒዓለም ቸርነትና የጻድቁ አባታችን የአቡነ ሓራ ድንግል ጸጋ የሚገለጽበት መሆኑን በመረዳ ት እንዲቋቋም ያስገነዘቡት በጸሎትም የተራዱት አቡነ ሓራ ድንግል ገዳም የሚገኙት ቅዱሳን ናቸው። ስሙንም የደነገጉት እነሱ ናቸው።
ማኅበርተኞች ማኅበሩ ከተመሠረተበት ዘመን ጀምሮ እስከ 2012 ዓም ድረስ ለስድስት ዓመታት ያህል በፈቃዳቸው የወር ተራ በመግባት የአምላካችንን የመድኃኒዓለምንና የጻድቁ አባታችንን የአቡነ ሓራ ድንግልን ወርሓዊ በዓላት በመዘከር ቆይተዋል። በየወሩ የሚከፍሉት መዋጮ እንዲሁም የመተዳደሪያ ደንብ አልነበራቸውም። ሆኖም የአርባ ሓራ ገዳም ሲታነጽ በመላው አሜሪካ የሚገኙትን በጎ አድራጊዎች በማስተባበር በርከት ያለ ገንዘብ በማሰባሰብ እጅግ ከፍ ያለ አስተዋፅዖ አበርክተዋል።
የአርብዓ ሓራ ገዳም ሕንፃ በሚያዚያ ወር 2010 ዓም ከተመረቀ በኋላ በገዳሙ የሚገኙ ቅዱሳን ማኅበሩ በአቡነ ሓራ ድንግል ስም ታላቅ ፈውስና በረከት የሚገኝበት ገዳም በቴክሳስ እንደሚያቋቋም ራዕይ ማየታቸውን አስታውቀው ማኅበርተኞች በትጋት እንድንነሳሳ አሳስበዋል። ፍጻሜውን ለማየትና የበረከቱ ተካፋዮች ለመሆን እየተመኘን ማኅበሩ ይህን ታላቅ ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ማኅበርተኞችን ማበራከትና የተጠናከረ መዋቅር እንደሚያስፈልግ ስለታመነበት ይህ የመተዳደሪያ ደንብ ተዘጋጅቷል።
ማኅበሩ፤ ምክርና በረከት እንዳይለየው አርብዓ ሓራ ድንገል ገዳም ከሚገኙ ቅዱሳን ጋር የቅርብ ግንኙነት ይቀጥላል።

<u>አንቀጽ ፩፤ የማኅበሩ ስምና አድራሻ</u>

፩፥፩ ከላይ በመግቢያው ላይ እንደተገለጸው የማኅበሩ ስም <u>**የአቡነ ሓራ ድንግል መድኃኔዓለም ማኅበር**</u> ሲሆን

1፡2 የማኅበሩ ማሕተም፣ ዙሪያ ቅርፅ ይዞ በመሀሉ የመድኅኒዓለም ሰዕል ያለበት ይሆናል።

አድራሻውም እንደሚከተለው ነው።

Monastery of Abuna Hara Dengeel

P.O. Box 850721

Richardson, TX 75081-0721

1፡3 ማኅበሩ እንደ አውሮጳውያን አቆጣጠር በወሩ የመጀመሪያው እሁድ የአምላካችንን የመድኃኔዓለምንና

የአባታችንን የአቡነ ኃራ ድንግለን ወርሐዊ በዓላት ለመዘከር የሚገናኘው በቅዱስ ሚካኤል ወቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን ነው። ሙሉ አድራሻውም እንደሚከተለው ነው።

**Mekane Selam St. Michael and St. Kidane Meheret Ethiopian Orthodox Tewahedo Church**
**1709 N Garland Ave, Garland, TX 75040**
**Phone: (469) 212 6370 *ወይንም* (214) 803 1347**

**<u>አንቀጽ 2፤ የማኅበሩ አመሠራረት</u>**

2፡1 ማኅበሩ የተቋቋመው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮችና በበጎ እርዳታ ሰጭዎች ሲሆን መርሆውም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ዶግማና ቀኖና ነው።

2፡2 የማኅበሩ ሕጋዊ ሰውነት የተደነገገውና የሚካተተውም በአሜሪካ አይ አር ኤስ ኮድ (IRS Code) 501(c)(3) በመሆኑ ከማዕከላዊ መንግሥት ታክስ ነፃ ነው።

2፡3 ማኅበሩ የሚመራው ማኅበርተኞች በመረጡት የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ሲሆን ኮሚቴውም በአርብዓ ሓራ ድንግል ገዳም ከሚገኙት ቅዱሳን ጋር የቅርብ ግንኙነት ያደርጋል።

2፡4 ጠቅላላ ጉባኤ የማኅበሩ የበላይ ጠባቂ ነው።

2፡5 ማንኛውም ግለሰብ ሆነ ድርጅት በክፍል (Section) 170(a)(2) መሠረት ታክስ እያስቀረጠ ለማኅበሩ ዕርዳት ማድረግ ይችላል።

2፡5 ማኅበሩም ከላይ በተጠቀሰው ኮድ መሠረት ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ጋር ትብብር አያደርግም።

**<u>አንቀጽ 3፤ የማኅበሩ የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድ</u>**

3፡1 በቅርብም ሆነ በሩቅ የሚገኙትን የመድኃኔዓለምን ወዳጆች በማኅበርተኝነት ይመዘግባል።

3፡2 እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር 2014 ዓም የማኅበርተኞችን ቁጥር 400 ለማድረስ ጥረት ያደረጋል።

3፡3 በየወሩ የመድኃኒዓለም ዕለት በመላው አሜሪካ የሚገኙት ማኅበርተኞች የሚሳተፉበት የጸሎት መርሐ ግብር በቴሌኮንፍረንስ ያካሄዳል።

3፡4 የመድኃኒዓለም ዝክር የሚዘከረው በፈረንጆቹ አቆጣጠር በየወሩ የመጀመሪያው እሁድ ነው። ሆኖም ችግር ካጋጠመ የመስተንግዶ ኮሚቴ ተስማሚ ቀን መርጦ ይቀይራል። ይህንንም ለማኅበርተኞች ያስታውቃል።

3፡5 በዓመት ሁለት ጊዜ የጥቅምትና የመጋቢት መድኃኔዓለምን በማሰብ አጠቃላይ ጉባዔ ያዘጋጃል።

3፡6 ከዳላስ ወጣ ብሎ በቴክሳስ ግዛት ውስጥ ሕመምተኞች የሚፈወሱበት፣ የተጨነቁ የሚጽናኑበት፣ ልጆች ደግሞ ሃይማኖታቸውን የሚያውቁበት ገዳም ያቋቁማል።

3፡7 የገዳሙ ግንባታ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ባለሙያ ያቀረበውን የግንባታ ወጭ መርምሮ በጠቅላላ ጉባኤ ያስወስናል።

3፡8 የገዳሙን ሥራ የሚከታተሉ ኃላፊዎችን የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ይሾማል።

**አንቀጽ 4፣ የማኅበሩ ራዕይና የወደፊት ዓላማዎች፤**

**4፡1** ***ራዕይ፤***

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮችንና ሌሎችንም በጎ አድራጊዎች አስተባብሮ፣ ሕመምተኞች የሚፈወሱበት፣ የተጨነቁ የሚጽናኑበት፣ ልጆች ደግሞ ሃይማኖታቸውን የሚማሩበት ገዳም ማቋቋም።

**4፡2** **ዓላማ፤**

ዓላማችንን፣ ራዕያችንን በመመርኮዝ በሥራ ላይ የምናውለውን ዕቅድ ታክቲክ እንዲሁም የሚያኮራ ባሕላዊ እሴቶቻችንን በመጠቀም የገዳሙን ሥራ ፈጽመን ምዕመናን ሲፈወሱ ማየት ነው።

**አንቀጽ 5፣ የማኅበርተኞች መብትና ግዴታ፤**

5፡1 ማንኛውም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ዕምነት ተከታይ አባል መሆን ይችላል።

5፡2 አንድ ማኅበርተኛ ሃየማኖትን ያልጠበቀ፣ ቂም በቀል ያለው፣ በማኅበርተኞች መካከል መቃቃር የሚፈጥርና ግዴታውን ያልተወጣ ከሆነ በማኅበርተኛነት መቀጠል አይችልም።

5፡3 ማንኛውም አባል በነፍስ ወከፍ፣ በወር በትንሹ $10 መክፈል ይጠበቅበታል። ባልና ሚስት ከሆኑ መዋጮአቸው $20 ይሆናል።

5፡4 አባላት በሥራ አስኪያጅ ወይም በንዑሳን ኮሚቴ በሚቀርብላቸው ጥሪ መሠረት አስተዋጽዖ ያበረክታሉ።


5፡5 ማንኛውም አባል በራሱ ፈቃድ በጽሑፍ አመልክቶ ከማኅበሩ መውጣት ይችላል

5፡6 ማንኛውም አባል በፈቃዱ ሆነ በማኅበሩ ከተሰናበተ ያዋጣው ገንዘብ አይመለስለትም።

**አንቀጽ 6፣ የማኅበሩ አደረጃጀትና መዋቅር፤**

ማኅበሩ ዓላማውን በተግባር ለመተርጎም የሚከትሉት ኃላፊዎችና ኮሚቴዎች ይኖሩታል።

ቻርት




**አንቀጽ 7፣ ሥልጣንና ኃላፊነት፤**

**7፡1**፣ የአባላት ጠቅላላ ጉባኤ

**7፡1፡1** የአባላት ጠቅላላ ጉባኤ የሚያመለከተው የማኅበሩን አባላት ምዕላተ ጉባኤ (51%) ነው።

7፡1፡2 በመጀመሪያው የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ የምላዐተ ጉባኤ ሳይሞላ ቀርቶ ስብሰባው ሳይካሄድ ቢቀር በሁለተኛው ጥሪ መሠረት የተገኙት ሰዎች ተሰብስበው ውሳኔ ይሰጡበታል።

**7፡1፡3** ጠቅላላ ጉባኤ፣ ሥራ አስኪያጅ አባላትን ይመርጣል። ተቆጣጣሪን ይሾማል።

**7፡1፡4** በዓመት ሁለት ጊዜ (መጋቢት 27 ወይንም ጥቅምት 27) የማኅበሩን ዕድገት ይገመግማል።

**7፡1፡5** ከዳላስ ውጭ የሚኖሩት አባላት ለመሰብሰብ አይገደዱም።

**7፡1፡6** ጠቅላላ ጉባኤ የሁሉም የበላይና የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ ነው።

**7፡1፡7** የማኅበሩን ተቆጣጣሪ ሪፖርት በማዳመጥ ውሳኔ ይሰጣል።

**አንቀጽ 8፣ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ፣**

**8፡1 የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ፣** ማኅበሩን በሥነ ሥርዓትና በሕጋዊ መንገድ ይመራል። በማኅበሩ ስም ውል ይዋዋላል። የገዳሙን አመሠራረት በበላይነት ይመራል።

**8፡2 ሙሴ/ሰብሳቢ፡-** ስብሰባዎችን ይመራል ሰነዶችን ይፈርማል። ሥራ አስኪያጆችንና ንዑሳን ኮሚቴዎችን በማስተባበር የማኅበሩን ዓላማዎች ያስፈጽማል።

**8፡3 ም/ሙሴ፡-** ዋናው ሙሴ በማይገኝበት ወቅት ሙሴውን ተክቶ ይሰራል።

**8፡4 ጸሐፊ፡-** ዋና ሥራው የማኅበሩን ሰነዶችን ይይዛል። ከሰብሳቢው ጋር በመመካከር አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፣ ስብሰባ ይጠራል፣ ቃለ ጉባኤን ይይዛል። ሰነዶችን በሙሴው ፊርማ ወጪ ያደርጋል።

**8፡5 ገንዘብ ያዥ፡-**በማኅበሩ ስም በደርሰኝ ገንዘብ ይቀበላል። የሰበሰበውን ገንዘብ በማኅበሩ የባንክ ሂሳብ በሦስት ቀን ውስጥ ገቢ ያደርጋል። ገንዘብ የሰበሰበበትን ደረሰኝና ባንክ ገቢ ያደርገበትን ማስረጃዎች ለሂሳብ ሹሙ ያስረክባል።

**8፡6 ሂሳብ ሹም፡-** የማኅበሩን ገቢና ወጪ ይመዘግባል። በየስድስት ወሩ ለሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል። ለማኅበሩ ቃል የተገቡትን ገንዘቦች መሰብሰባቸውን ያረጋግጣል። የማኅበሩን የባንክ ሂሳብ በየውሩ ያመሳክራል።

**8፡7 የመስተንግዶ ኮሚቴ፤** አባላትን ተራ በማስያዝ በየወሩ የመድኃኒዓለምንና የአቡነ ሓራ ድንግልን በዓላት ይዘክራል። ጠቅላላ ጉባኤ በሚኖርበት ጊዜ ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ጋር በመመካከር እንደ አስፈላጊነቱ አባላትን ያስተባብራል።

**8፡8 የማኅበራዊ ግንኙነት፡-** በአባላት መካከል መቀራረብና መተሳሰብ እንዲኖር ማድረግ። ማኅበርተኞችን ስለ ደህንነታቸው መጠየቅ። ማኅበርተኞች ንቁ ተሳትፎ እንዲአደርጉ ማነቃቃት።

**8፡9 ተዐምር ወመዘከር፣** በጻድቁ አባታችን አማላጅነት፣ በመድኃኔዓለም ምህረትና ቸርነት፣ የተፈወሱትን ምዕመናን ታሪክ መዝግቦ በልዩ ልዩ ዘዴዎች ለሕዝበ ክርስቲያን ማዳረስ።

**8፡10 የማኅበሩ አጠናካሪ ኮሚቴ፤** ዋና ዓላው በ2014 የማኅበርተኞችን ቁጥር እስከ 400 ማድረስ ነው።

ማኅበሩ ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን የገንዘብ አቅም በልዩ ልዩ ዘዴዎች ማጎልበት።

**አንቀጽ 9 ተቆጣጣሪ** ፡- በየሦስት ወሩ ሂሳብ መመርመርና ለሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ሪፖርት ማቅረብ እንዲሁም በጥቅምትና በመጋቢት ወራት ስለማኅበሩ አቋምና የሥራ እንቅስቃሴ ለአጠቃላይ ጉባኤው ግምገማ ያቀርባል። ይኸውም የማኅበሩ የሥራ አስኪያጆችና ኮሚቴዎች በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ሥራቸውን ማከናወናቸውን ያረጋግጣል።

**አንቀጽ 10፣ የመገናኛ ዘዴዎች፤**

**10፡1** በኢሜል MOAHara27@gmail.com

**10፡2** በቴሌኮንፍረንስ ቁጥር፣ (425)436 6349፤ ኮድ፣ 163854#

**10፡3** በስልክ፣ በቴክስት፣ (ቫይበር) ለጊዜው የተመረጠ ነው።

**10፡4** ድሕረ ገጽ ወይንም ዌብ ሳይት፣ www.moahara.com

**አንቀጽ 11፣ ማጠቃለያ፤**

**11፡1** ማኅበሩ አገልግሎቱን ቢያቋርጥና መቀጠል ባይችል በማኅበሩ ስም የተመዘገበ ንብረት ሁሉ በአሜሪካን ሀገረ ስብከት ለተመዘገበ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ይሰጣል።

**11፡2** የማኅበሩ ሥራ አስኪያጆች ወይንም ማናቸውም በፈቃደኝነት ተመርጠው የሚያገለግሉ የድካም ዋጋ አይከፈላቸውም።

**11፡3** የማኅበሩ አገልጋዮች ከግል ጥቅማቸው ጋር በተያያዘ መንገድ በማኅበሩ ስም ግዢ መፈጸም ወይንም የገንዘብ ወጪ ማድረግ አይችሉም።

**11፡4** ይህን ደንብ ማሻሻል የሚቻለው ሁለት የሥራ አስኪያጆች ወይንም አሥር በመቶ (10%) አባላት የደገፉት የማሻሻያ ሀሳብ በጽሑፍ ለጸሓፊው ሲቀርብና ጸሓፊውም ለጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ ሲያቀርብ ነው።

**የመተዳደሪያ ደንብ አውጪ ኮሚቴ ፊርማ።**

1ኛ፣ አቶ አፈወርቅ ተገኝ። ______________________ ቀን፣______________

2ኛ፣ አቶ በቀለ ተክሌ______________________ ቀን፣______________

2ኛ፣ አቶ ብርሃነማርቆስ ታደሰ______________________ ቀን፣______________

4ኛ፣ ወ/ሮ የውብዳር ከሊፋ______________________ ቀን፣______________

5ኛ፣ አቶ ተመስገን ይርሳው______________________ ቀን፣______________